Amsterdam UMC

አምስተርዳም UMC
መልካም የማህፀን ሕክምና

# ቂንጥር (Amharic vertaling)

Locatie AMC

ይህ በራሪ ወረቀት ከሴት ልጅ ግርዛት በኋላ ስለ ቂንጥር ግንባታ መልሶ ማስተካከያ ይዟል። ይህንንም "የማስተካከያ ቀዶ ጥገና" ብለን እንጠራዋለን። በዚህ ብሮሹር ውስጥ በቀዶ ሕክምና ሂደት ላይ እናተኩራለን።

**ቀዶ ጥገናው ለማን ነው የታሰበው?**

የማስተካከያ ቀዶ ጥገና በዋናነት ለተገረዙ ሴቶች ነው። የሴት ብልት ካንሰር ያለባቸው ሴቶችም የማስተካከያ ቀዶ ጥገና ሊደረግላቸው ይችላል። ከ 2010 ጀምሮ በኔዘርላንድ ውስጥ ወደ 50 የሚጠጉ ሴቶች የማስተካከያ ቀዶ ጥገና አካሂደዋል። በዓለም ዙሪያ ከ 10,000 በላይ ሴቶች ናቸው።

አምስተርዳም UMC በኔዘርላንድ ውስጥ ለሴት ልጅ ግርዛት የተመደቡ የባለሙያዎች ማዕከል ነው። ለምክር እና ለህክምና/ቀዶ ጥገና ወደ እኛ መምጣት ይችላሉ።


**ማሳሰቢያ፡ ቂንጥርን መልሶ ማስተካከል በቀዶ ጥገና ከመክፈት ጋር አንድ አይነት አይደለም።**

በቀዶ ጥገና መክፈት የሴት ብልትን ቀዳዳ ማስፋትን ያካትታል። በጣም አስከፊ የሆነ የሴት ልጅ ግርዛት (infibulation) የተፈጸመባት ሴት "እንደገና ይከፈታል። ይህ ከቂንጥር መልሶ ማስተካከል የተለየ ነው።

**ቂንጥር**

**የተገረዙ ሴቶች ቂንጥር አላቸው?**

አዎ፣ የተገረዙ ሴቶች አሁንም ቂንጥር አላቸው። ከውጭ ከሚታየው "ጫፍ" በጣም ትልቅ ነው። አብዛኛው ቂንጥር በሰውነት ውስጥ ነው ያለው፤ (ሥዕሉን ይመልከቱ)። በግርዛት ወቅት የሚታየው የቂንጥር ክፍል ተቆርጧል። ቀሪው ሳይበላሽ ይቀራል። ይህ በውጭ ሊታይ አይችልም፤ ነገር ግን አሁንም አለ።




**ምን አይነት የሴት ብልት ግርዛት አለ?**

<u>የአለም ጤና ድርጅት 4 የሴት ልጅ ግርዛትን ይገልፃል።</u>

ዓይነት I

ከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ (የሚታየውን ክፍል) ቂንጥርን ማስወገድ ወይም ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች በቂንጥር ዙሪያ ያለውን የቆዳ እጥፋት ብቻ (ክሊቶሪዲክቶሚ)።

ዓይነት II


የቂንጥሬን እና የትንሽ ከንፈሮችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ (የሚታየውን ክፍል) ነገር ግን ትላልቅ የብልት ከንፈሮች ሊነኩም ላይነኩም ይችላሉ።

ዓይነት III

ቂንጥርን በማንሳትም ሆነ ባለማንሳት ትንንሽ ወይም/እና ትልልቅ የብልት ከንፈሮች ጋር በመቁረጥ እና አንድ ላይ በማገናኘት የሴት ብልት ቀዳዳን ማጥበብን ይመለከታል።

ዓይነት IV

በሴት ብልት የአካል ክፍሎች ላይ ማንኛቸውም ሌሎች ከህክምና ውጭ ለሆኑ ምክንያቶች  የሚደረጉ ጎጂ ድርጊቶች ያካትታል። ለምሳሌ መብሳት ፣ መቅረጽ ፣ መቧጨር እና መቁረጥ የመሳሰሉ ናቸው።




"እንደገና እንደ ሴት እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ፤ የሆነ ነገር አለ
የተወሰደበኝና እና ያንን መመለስ እፈልጋለሁ። ሙሉነት አይሰማኝም።"

**ቀዶ ጥገናው**

**ቀዶ ጥገናው ምንን ያካትታል?**

ቂንጥርን በመልሶ  ማስተካከል ላይ፣ በሰውነት ውስጥ በጥልቅ ውስጥ የሚገኘውን ቂንጥርን ወደ ላይ እናመጣለን። የማህጸን ስፔሻሊት ሐኪሙ በመጀመሪያ በግርዛት የተፈጠረውን ጠባሳ ያስወግዳል። ከዚያም ቂንጥሬው ይለቀቃል፤ ወደ ፊት ቀረብ ይደረግና እና በአዲሱ ቦታ ይሰፋል። አንዳንድ ጊዜ ቂንጥር በሴት ብልት ውስጥ ከውስጥ በሚመጣ

መከላከያ ሽፋን የተሸፈነ ነው። አብዛኛዎቹ ሴቶች ይህንን ሳይሸፈኑ መተው ይመርጣሉ፣ ስለዚህ (ሮዝ) መልክ በኋላ ላይ ብዙም አይታወቅም።

**የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪም የብልት ከንፈርን መስራት ይችላል?**

አዎ፣ ትችላለህ። ብዙውን ጊዜ የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ሐኪም ከማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪም ጋር አብሮ ይሠራል። አዲሱን የብልት ከንፈር ለመሥራት የፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ሐኪሙ ከመቀመጫዎች አንድ ቁራጭ ቆዳ ይጠቀማል። አብዛኞቹ ሴቶች የብልት ከንፈርን ሳይሆን ቂንጥርን ብቻ ለመመለስ ይመርጣሉ።

**ቂንጥር ከቀዶ ጥገና በኋላ "የተለመደውን" ቂንጥር ይመስላል?**

የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪሙ በተቻለ መጠን ቂንጥርን ወደ ተለመደው ቂንጥር በተቀራረበ መልኩ እንደገና ለመፍጠር ይሞክራል። ይሁን እንጂ 100% አንድ አይነት አይመስልም። ሁልጊዜም ጠባሳ ማየትዎን ይቀጥላሉ።

**ለቀዶ ጥገናው ከፍተኛ ዕድሜ የምባል አለ?**

አይ የለም፤ ለማስተካከያ ቀዶ ጥገና ከፍተኛ ዕድሜ የምባል የለም፤ ዕድሜያቸው 18 የሆኑ ሁሉም ሴቶች ብቁ ናቸው።

**ለቀዶ ጥገናው ሰመመን ውስጥ መግባት አለብኝ?**

አዎ፤ ሙሉ ሰመመን ይመከራል። ይህ እንደገና የግርዛት ስሜት አይነት እንዳይሰማሽ ይከላከላል። እንዲሁም በከፊል ማደንዘዣ (epidural) መምረጥ ይቻላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ካንቺ ጋር ለመወያየት እና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ሁል ጊዜ ከማደንዘዣ ባለሙያ ጋር ቀጠሮ ይኖረኛል።

**ቀዶ ጥገናው ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

የማስተካከያ ቀዶ ጥገና በጣም ቀላል ሂደት ነው፤ በአማካይ ከ 45 ደቂቃዎች እስከ 1 ሰዓት ይወስዳል። የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪሙ ትንሽ የብልት ከንፈር ካደረገ  ቀዶ ጥገናው ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል: ከ 1.5 እስከ 2 ሰአታት የሚያህል ይወስዳል።

**ፎቶግራፎች ይነሱ ይሆን?**

አዎ፤ ፎቶግራፎች ከመልሶ ማስተካከያ ቀዶ ጥገና በፊት እና በኋላ ይወሰዳሉ። እነዚህ በተጠበቀ ሁኔታ ወደ ህክምና መዝገብዎ ውስጥ ይገባሉ።

**በቀዶ ጥገናው ስሜቴን መልሼ አገኛለሁ?**

ይህ በፍፁም ዋስትና ያለው ነገር አይደለም። የጾታዊ ግንኙነት ልምድ በስነ-ልቦና፣ በማህበራዊ እና በባህላዊ ሁኔታዎች ይወሰናል፤ ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አብዛኞቹ ሴቶች በጾታዊ ግንኙነት ጊዜ በቂንጥር የመደሰት መሻሻል ይታይባቸዋል።

"አንዳንድ ሴቶች ቀዶ ጥገና (ወዲያውኑ) አይደረግላቸውም፤ ምክንያቱም ለምሳሌ በቀዶ ጥገናው ውጤት ላይ የማይጨበጥ ተስፋ ስላላቸው ወይም በመጀመሪያ መታከም ያለባቸው የስነ-ልቦና ችግሮች አሉ።"

**ከቀዶ ጥገና በኋላ ቂንጥሬ ያማል?**

አዎ፣ ከቀዶ ጥገናው በኋላ ወዲያውኑ ቂንጥርዎ ከመጠን በላይ ስሜታዊ ሊሆን ይችላል። ጠባሳውም ሊጎዳ ይችላል።

**ነገሮች የመባባስ እድል አለ?**

አዎን፣ እንደ ማንኛውም ቀዶ ጥገና, ሁልጊዜም ነገሮች የመባባስ እድል አላቸው፣ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከ 5 እስከ 15% ከሚሆኑ የቀዶ ጥገናዎች ላይ ውስብስብ ችግሮች የመከሰት እድል አለ። እነዚህም እብጠት፣ ደም መፍሰስ፣ የስፌት መፈታት እና መጠነኛ ትኩሳት ናቸው። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ቀላል ችግሮች ከጥቂት ጊዜ በኋላ በራሳቸው ይጠፋሉ። ነገር ግን አልፎ አልፎ, ሌላ ቀዶ ጥገና ሊያስፈልግ ይችላል።

**ሴቶች የማስተካከያ ቀዶ ጥገና ለምን ይፈልጋሉ?**

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴቶች በዋነኛነት የበለጠ የሴትነት ስሜት እንዲሰማቸው ይፈልጋሉ። በተጨማሪም, የወሲብ ተግባራቸውን ለማሻሻል እና ትንሽ ህመም (በወሲብ ወቅት) እንዲኖራቸው ብቻ ይፈልጋሉ።

**ሴቶች በቀዶ ጥገናው ደስተኛ ናቸው?**

ሴቶች በአጠቃላይ አዎንታዊ ምላሽ አላቸው፤ በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ የበለጠ ሴትነት ይሰማቸዋል፤ በራስ የመተማመን ስሜት ይጨምራል፤ ህመም አይሰማቸውም እና በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ የበለጠ ይደሰታሉ። ቀዶ ጥገናውን (84%) በማግኘታቸው በጣም ደስተኛ ናቸው። በቀዶ ጥገናው ቅር የተሰኙ ሴቶችም አሉ።

**የማስተካከያ ቀዶ ጥገና ካርታ**

1. <u>ጠቅላላ ሐኪም</u> ፡ ለማስተካከያ ቀዶ ጥገና ያለዎትን ፍላጎት በመጀመሪያ ከጠቅላላ ሀኪምዎ ጋር ይወያዩ። የቤተሰብ ዶክተር የሪፈራል ደብዳቤ ይሰጥዎታል። ይህ አስቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ ክሊኒካችንን በቀጥታ ማግኘት ይችላሉ እና ከእርስዎ ጋር እንሰራለን።

2. <u>ቅ:</u> ከቀዶ ጥገናው በፊት ብዙ ጊዜ ብዙ ንግግሮች ታደርግያለሽ። የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪሙ ምኞቶችዎ እና ተስፋዎችዎ ምን እንደሆኑ ይጠይቃል። የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪሙ ስለ ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎ፣ ስለ አጠቃላይ የአካል ሁኔታዎ እና ስለ ወሲባዊ ተግባርዎ ጥያቄዎችን ይጠይቃል። በመግቢያው ወቅት, የቀዶ ጥገናው መሆን አለመሆን እድል በደንብ ይብራራል።

በመግቢያው ወቅት ቁልፍ ሰው/ተርጓሚ መገኘት ብችል ጥሩ ነው። ይህ ሰው እንዲረዳዎትና እና ለእርስዎ እንዲተረጉም (አስፈላጊ ከሆነ) ነው። ለትርጉም ካልፈለጉ ወይም ምንም ፍላጎት ከሌለዎት ይህ በእርግጥ ግዴታ አይደለም።

3. <u>የአካል ምርመራ</u> ፡ የአካል ምርመራ ታደርግያለሽ። ስለ ተደረጉ ነገሮች ጥሩ ማብራሪያ ይሰጥዎታል፤ በተለይም በመስተዋት የተደገፈ ቢሆን ጥሩ ነው። ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉዎት? ከሆነ, እኛ ለእነሱ መልስ ለመስጠት ደስተኞች እንሆናለን።
4. <u>ሌሎች ስፔሻሊስቶችን ማማከር</u> ፡ የስነ ልቦና፣ የአካል ወይም የወሲብ ችግሮች አሉብሽ? ከሆነ፣ ከሴክስሎጂስት እና/ወይም ከስነ-ልቦና ባለሙያ ጋር የተለየ ቀጠሮ ይይዛሉ። በቅበላው ወቅት ይህንን ፕሮግራም ከማንኛውም የቀዶ ጥገና ሂደቶች ጋር በአንድ ጊዜ እንደምናስኬደው ከእርስዎ ጋር እንወስናለን ። ወይም በመጀመሪያ ከሴክኮሎጂስት እና/ወይም ከስነ-ልቦና ባለሙያ ጋር፣ ለምሳሌ ከባድ የPTSD ህመሞች ካሉ የተሟላ የህክምና ፕሮግራም ማለፍ ብልህነት ነው።
5. <u>ግምገማ</u> ፡ ለቀዶ ጥገናው ብቁ ከሆኑ ይነገርዎታል። አንዳንድ ጊዜ ቀዶ ጥገና (በዚህ ጊዜ) ለችግሮችዎ ትክክለኛ መፍትሄ ላይሆን ይችላል።
6. <u>በመረጃ የተደገፈ ስምምነት</u> ፡ ከቀዶ ጥገናው በፊት ስለ አማራጮችዎ፣ ገደቦችዎ እና የችግሮች ስጋቶች መረጃ ይሰጥዎታል። ከዚያ ለቀዶ ጥገናው ፈቃድ ይሰጣሉ።
7. <u>በምርምር ውስጥ መሳተፍ</u> ፡ የእኛን እንክብካቤ የተሻለ እና የተሻለ ለማድረግ በሳይንሳዊ ምርምር ላይ መሳተፍ ከፈለጉ እንጠይቅዎታለን። በምክክሩ ላይ ስለዚህ ጉዳይ የበለጠ እናብራራለን።
8. <u>የቀዶ ጥገና ቀን እና ቀጠሮ ከማደንዘዣ ባለሙያ ጋር:</u> ቀዶ ጥገናው ሊቀጠር ይችላል፤ እንዲሁም ስለ ማደንዘዣ ወይም ስለ epidural የበለጠ ለመወያየት ከማደንዘዣ ባለሙያው ጋር ቀጠሮ ይኖራችኋል።
9. <u>ቀዶ ጥገና</u> ፡ ቀዶ ጥገና ይደረግልዎታል ብዙውን ጊዜ ቀዶ ጥገናው በቀን ቀዶ ጥገና ላይ ነው። በመርህ ደረጃ በተመሳሳይ ቀን ወደ ቤት መሄድ ይችላሉ። የትንሽ ብልት ከንፈር ማስተካከል ከፈልጉ ሆስፒታል ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ። ይህንን በደንብ ያቅዱ እና አንድ ሰው እንዲወስድዎት ያድርጉ።
10. <u>የቀዶ ጥገና ማገገሚያ ሂደት</u> ፡ ከቀዶ ጥገና በኋላ ከቀዶ ጥገና ምን ምን ማድረግ እንዳለብዎት የያዘ በራሪ ወረቀት ይደርስዎታል፣ እባክዎን በጥንቃቄ ያንብቡት። ቁስልዎ ማገገም አለበት ፣ ይህንን ሲያደርጉ በተቻለዎት መጠን ማረፍ አለብዎት። ህመሙን ለማስታገስ በሐኪም የታዘዙ የህመም ማስታገሻዎች ይሰጥዎታል። የሚጠበቀው የማገገሚያ ጊዜ ብዙውን ጊዜ በ6-12 ሳምንታት መካከል ነው። በትክክል ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ብዙውን ጊዜ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል። (በተጨማሪ በምዕራፍ መልሶ ማገገሚያ ሂደት ውስጥ ይመልከቱ)
11. <u>ምርመራዎች</u> ፡ ብዙ ጊዜ ከ10 ቀናት በኋላ ይጠራሉ እና ከ3 ሳምንት - 3 ወር - 6 ወር እና ከ1 አመት በኋላ ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ይመጣሉ።

**የቁልፍ ሰው/ተርጓሚ/አጋሮች ሚና፡-**

በምክክር ክፍሎች ውስጥ እንደተሰማሽ፣ እንደተረዳሽ እና ደህንነትሽ እንዲሰማሽ አስፈላጊ ነው። ሁልጊዜ አጋሮችን ልታመጣ ትችያለሽ፣ እና ቁልፍ የሆነ ሰው መሳተፉ ብዙ ጊዜ ጥሩ ነው። ቁልፍ ሰው ሊረዳዎ የሚችል የሰለጠነ ባለሙያ ነው።

አንድ ቁልፍ ሰው ብዙ ጊዜ ከእርስዎ ጋር ወደ ቀጠሮዎችዎ ላይ ይመጣል ለምሳሌ በቅበላ ጊዜ ቁልፍ ሰው ብዙውን ጊዜ ከእርስዎ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ አለው እና በሂደቱ ውስጥ ብዙ ጊዜ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎን ይናገራል። ቁልፍ ሰው ብዙ ወሳኝ ሚናዎችን ያከናውናል።

1. አስተማሪ፣ ደጋፊ እና ጓደኛ፡ ቁልፍ ሰው በቀጠሮው ወቅት ስሜታዊ ድጋፍ ሊሰጥዎት ይችላል። ይህ እርስዎን ማረጋጋት፣ ከሐኪምዎ ጋር መነጋገርን ማበረታታት እና በሂደቱ ወቅት አጠቃላይ መመሪያ መስጠትን ሊያካትት ይችላል።

2. አስታራቂ፡- እርስዎ እና ዶክተርዎ ብዙ ጊዜ ከተለያየ አስተዳደግ የመጡ ሊትሆኑ ትችላላችሁ። ስለዚህ ሁለቱንም ባህሎች የሚያውቅ ሰው ማግኘት ጥሩ ነው። ስለዚህ ለሁለቱም ወገኖች የባህል ልዩነቶችን (ልዩነቶችን/አውድ) ማስረዳት እና አለመግባባቶችን ማስወገድ ይችላሉ።
3. ለእርስዎ ተሟጋች፡ ቁልፍ ሰው እርስዎ እንዲሰሙዎት፣ ምኞቶችዎ እና ስጋቶችዎ እንደተረዱ እና መብቶችዎ መከበሩን ማረጋገጥ ይችላል።

መተርጎም፡- አንዳንድ ጊዜ በደች ወይም እንግሊዘኛ ችሎታ ከሌለህ አስተርጓሚ ያስፈልጋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቁልፍ ሰው በዋናነት አስተርጓሚ ሲሆን በሌሎች ሁኔታዎች አስተርጓሚ በስልክም ሆነ በአካል ልናዘጋጅ እንችላለን። ይህ ሰው ሴት እንድትሆን እንተጋለን፤ ነገር ግን ይህ ሁልጊዜ የሚቻል አይደለም።

ከቁልፍ ሰው (ወይም አስተርጓሚ) ጋር እምነት የሚጣልበት ግንኙነት እንዲኖርዎት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ልምዱን ውጥረት እንዳይኖረው ለማድረግ ይረዳል፤ በእርስዎ እና በተንከባካቢዎች መካከል ግንኙነትን ቀላል ያደርገዋል። ካልተመቸዎት እባክዎ ይህንን ወዲያውኑ ያመልክቱ። በዚህ ረገድ ልንረዳዎ እና ልንረዳዎ እንችላለን።

## የማገገሚያ ሂደት

### በሆስፒታል ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት አለብኝ?

ቀዶ ጥገናው ብዙውን ጊዜ የአንድ ቀን ቀዶ ጥገና ነው። ጠዋት ላይ ቀዶ ጥገና ይደረግልዎታል እና ምሽት ወደ ቤትዎ እንዲሄዱ ይፈቀድልዎታል። እርስዎ የትንሹ የብልት ከንፈር ማስተካከል ከፈለጉ፣ አንዳንድ ሴቶች ለአንድ ቀን ሆስፒታል ውስጥ ይቆያሉ።

### ለምን ያህል ጊዜ ማረፍ አለብኝ?

ቁስሉ አንድ ሳምንት ሙሉ እረፍት ሊኖረው ይገባል። ስለዚህ በመጀመሪያው ሳምንት ውስጥ በተቻለ መጠን ነገሮችን ቀለል ማድረግ አለብዎ። ሻይ መጠጣት ወይም ሻወር መውሰድ ጥሩ ነው። ነገር ግን ለምሳሌ ወደ ገበያ አይሂዱ፣ ልጆቹን ከትምህርት ቤት አይውሰዱ፣ በብስክሌትዎ አይንዱ፣ ምግብ አያብስሉ፣ አይዋኙ ወይም አይታጠቡ። በሚቀጥሉት ሳምንታት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎን ቀስ በቀስ መቀጠል ይችላሉ። ቢያንስ ለስድስት ሳምንታት ቀለል ያሉ ነገሮችን ብቻ ያድርጉ እና ምንም አይነት ከባድ የአካል ስራ አይስሩ። ለምሳሌ, በቤት ውስጥ ስራዎች እርዳታ ይጠይቁ።

### መድሃኒት ይሰጠኛል?

ከቀዶ ጥገናው በኋላ በመጀመሪያዎቹ 6 ሳምንታት ቁስሉ ስስና እና ህመም ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ, ሽንት ስሸኑና እና በእግር ሲራመዱ ህመም ሊኖር ይችላል። ለህመም ማስታገሻ እና ምናልባትም ቅባት የመድሃኒት ማዘዣ ይሰጥዎታል። ቂንጥር እንዳይደርቅ ማድረግዎን እርግጠኛ ይሁኑ። እንዲሁም ቁስሉን ንጹህ ያድርጉት።

### ማገገም ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

የቀዶ ጥገና ቁስሉ ሙሉ በሙሉ ለመዳን ከ 6 እስከ 12 ሳምንታት ይወስዳል። በትክክል ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አስቀድሞ መናገር አይቻልም፤ ከሰው ወደ ሰው ይለያያል።

### እንደገና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የምችለው መቼ ነው?

ቁስሉ ሙሉ በሙሉ እስኪድን ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመፈጸም ብልህነት ነው። ስለዚህ ከ 6 እስከ 12 ሳምንታት በኋላ።

### ምን ዓይነት ችግሮች ሲኖሩ መደወል አለብኝ, የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

- የሽንት ለመሽናት መቸገር፤ ሽንት አይመጣም፣ በጣም ያማል ወይም ይሸታል::
- ትኩሳት (ከ 38.5 ዲግሪዎች ወይም ከዚያ በላይ)
- ቁስሉ በድንገት በጣም ያማል ወይም በጣም ያሠቃያል።
- ቁስሉ ቀይ ወይም ወፍራም ከሆነ፣
- ቁስሉ የምደማ ከሆነ፣
- ቁስሉ በጣም መጥፎ ሽታ ካለው ወይም መግል እየወጣ ከሆነ፣
- የሚሰማዎት ነገር የተለመደ ስለመሆኑ ከተጠራጠሩ በማንኛውም ጊዜ ማማከር ይችላሉ።

### ለምርመራ መቼ መምጣት አለብኝ?

እንዴት እንደሆኑ ለማወቅ ከ10 ቀናት በኋላ በስልክ ይደልላለሸዋል። ከ 3 ሳምንታት በኋላ, ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ለምርመራ ይመለሳሉ። የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪሙ ራሱ ከ 3 ወር በኋላ ፣ ከ 6 ወር በኋላ እና ከ 1 ዓመት በኋላ እንደገና ሊያገኝዎት ይፈልጋል ። ቅሬታዎች ካሉዎት, በእርግጥ ቀደም ብለው ያነጋግሩታል።

**የቤተሰቤ ሐኪም እንዲሁ ማሳወቂያ ይደርሰዋል?**
አዎን፤ በኮርሱ መጨረሻ ላይ, የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪም ሁል ጊዜ ሁሉንም መረጃዎች ለዶክተርዎ ደብዳቤ ይልካል። ይህን **ካልፈለክሽ** ፤ እባክህ ንገረን። ያኔ ይህን አናደርግም።

**ወጪ**
**የቀዶ ጥገናው ዋጋ ስንት ነው?**
የማስተካከያ ቀዶ ጥገና ዋጋ በሂደቱ መጠን ይወሰናል።
**የጤና ኢንሹራንስ የቀዶ ጥገናውን ወጪ ይከፍላል?**
እስከዛሬ ድረስ በኔዘርላንድ ውስጥ የማስተካከያ ቀዶ ጥገና የሚከፈለው በጤና ኢንሹራንስ ኩባንያ በሕክምና ምክንያት (አካላዊ ቅሬታዎች) ብቻ ነው። ይህ ማለት በአንዳንድ ሁኔታዎች የቀዶ ጥገናው በጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ይከፈላል ማለት ነው። ይህንን ከማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪም እና ከጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ ጋር በጥንቃቄ ያረጋግጡ።
ያለ ቀዶ ጥገና ህክምና የምክር አገልግሎት ብቻ ቢያገኙም ተቀናሹን መክፈል እንዳለቦት ማስታወስ አለብዎት። ለቀጠሮዎች የማጓጓዣ ወጪንም ይጠብቃሉ።
**ተጨማሪ መረጃ?**
ስለ ቂንጥር መልሶ ማስተካከል የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ? ተጨማሪ መረጃ በአምስተርዳም UMC ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።
ወይም የእኛን ልዩ ቡድን በቀጥታ በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ፦
ስልክ ቁጥሮች (በሳምንቱ ከጠዋት 2:00 እስከ ማታ 11:00 ባለው ጊዜ ውስጥ ይገኛሉ)፦
አጠቃላይ የማህፀን ህክምና የተመላላሽ ታካሚ: 020-5661601
ስለ የሴት ልጅ ግርዛት እንክብካቤ ጥያቄዎች ስልክ ቁጥር 020-5667525
(መልስ ከሌለ እባኮትን ከስምዎ እና ከስልክ ቁጥርዎ ጋር የድምጽ መልእክት ይተዉ እና ለእርስዎ ይደውልሎታል)
ኢሜል : VGV@amsterdamumc.nl